# <u>ዲሞክራሲያውያን ሕብረት ተጋሩ ሰሜን አመሪካ</u>

## <u>ሰንካላው የአልጀርስ ስምምነት ትናንትም አልበጀም ዛሬም አይበጅም</u>

ከኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት፣ የአገሪቷን ሉአላዊነት ፣ ጥቅምና ዘላቂ ሰላም ለአደጋ ያጋለጠው የአልጀርሱ ስምምነት እስከነአካቴው ውድቅ የሚሆንበት ሁኔታ ዳግም ተፈጥሯል:: ሰሚና ተቆርቋሪ መንግስት ቢገኝ::

ሻዕብያ በታንክና በመሳርያ ታጅቦ የአልጀርሱ ስምምነት ዋነኛና መሰረታዊ አካል የሆነውን የፀጥታ ቀጠና ጥሶ ወደ ኢጥዮጵያ ደንበር በመጠጋት ሰራዊቱን አስፍራል:: የፀጥታ አክባሪ ሃይሉ (UNMEE) ጥሰቱን በግልፅ ለሚመለከተው ሁሉ ሪፖርት አድረጓል:: ተከታትሎም የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሃፊ ኮፊ አናን እንዲሁም የፀጥታው ምክርቤት የኤርትራን ሕገውጥ ድርጊት (Violation) በመኮነን የአልጀርሱ ስምምነት በከፍተኛ ደረጃ እንደጣሰች (Major Breach) በማያሻማ ቋንቋ ግልፅ አድርጓል::

ዩስ አመሪካና ታዛቢ ሶስተኛ ወገኖችም የሻዕብያ ትንኮሳ፣ የፀጥታ ቀጠና መድፈሩንና የስምምነቱን መጣስ ካለምንም ማመንታት ሲያወግዙና ባስቸካይ ኤርትራ ወታደሮቿን እንድታስወጣ ሲወተውቱ የተገላቢጦሽ የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ጉዳዩን በማሳነስና በማንኳሰስ (Minor Provocation) በማለት አጣጥለውታል::

ባለፈው የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናትና የስለላ ባለሙያዎች እንዲሁም የጠረፉ ነዋሪ ህዛባችን ሻዕብያ እንደሚወረንና ለዚሁ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አለብን በሚሉበት ጊዜ አቶ መለስ <u>የጠላቤት ወሬ ነው ብለው</u> ሳንዘጋጅ በሻዕብያ እንድንወረር ማድረገቸው የኢትዮጵያ ህዝብ አይረሳውም:: ሻዕብያ እንደገና ባድመ፣ አሊተናንና ዛላምበሳን መልሶ እስኪወስድ እየጠበቁ እንደሆነ እንጂ ሌላ ጤናማ ምክንያት ይኖራቸዋል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል::

ሻዕብያ የሶማልያ ሽብርተኞችንና አክራሪዋችን እንደሚያሰለጥንና እንደሚያ ስታጥቅ፣ በኢትዮጵያ የአገር ውስጥ ጉዳይም ጣልቃ በመግባት የተለያዩ ሃይሎችን ለሽብርና ለጦርነት እንደሚያዘጋጅ የአደባባይ ሚስጥር ነው::

በየእለቱ የፀጥታ ቀጠና በመጣስም ይሁን ድንበር ዘለል ሽብርን በማስፋፋት እነ አመሪካና የተባበሩት መንግስታት ሲከሱትና ሲኮኑኑት አንድም ቀን የጠቅላይ ሚ/ር መለስ ምንግስት ጉዳዩ ለፀጥታ ምክር ቤት ለማቅረብ ሞክሮም አያውቅም::

ላለፉት ስድስት ሰባት አመታት ከቀላል እስከ ከባድ እረፍት የሌለው ጥሰት ሳይታረም መከማቸቱ ሳያንስ አሁን የውሉ ዋና መሰረትና ዋልታ የሆነው የፀጥታ ቀጠና በሻዕብያ ድርጊት ሙሉ በሙሉ ፍርሽ ሆናል::

ከዚህ በኋላ አቶ መለስ የቱን ይዘውና ተንጠልጥለው የአልጀርስ ስምምነቱን ሊያቆዩት እንደሚፈልጉ ሊገባን አይችልም::

በኢትዮጵያ ህዝብ ወገን ግን ይህ አልጀርስ ስምምነት ድሮም ለኤርትራ ያዳላ ሰንካላ ነው:: አሁንም አልቆለታል:: ካሁን በኋላ ሻዕብያ የገደለውን የአልጀርሱ ስምምነት (ውል) አቶ መለስ ነፍስ ሊዘሩበት ባይሞክሩ ይበጃቸዋል::
ስለሆነም መላው የኢትዮጵያ ህዝብና ሰላም ፈላጊው የአለም ህብረተሰብ አቶ መለስ እና ተከታዮቻቸው የሚከተሉት አደገኛ መንገድ ለህዝባችንና ለአገራችን የሚጠቅም ባለመሆኑ፣ እነሱም ከሃላፊነት እንዳያመልጡ እንዲያጋልጣቸውና እንደወትሮው እንዲታገላቸው ለሰላም ወዳዱ ህዛባችን እናሳስባለን::